# አባይ ድሮ አባይ ዛሬ

- *ታላቁ የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ሲቃኝ*

Sofia Teshome May 16, 2011

አባይ ታላቅ ወንዛችን ነው። በዓለም ላይ የሀገራችንን ስም ካገነንዋት ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ሃብቶቻችን መካከል የዚህ የታላቅ ወንዝ -ዓባይ (Blue Nile) - ምንጭና ባለቤት መሆናችን ጎልቶ ይጠቀሳል። በመሆኑም ለዘመናት - በቁጭት - በፖለቲከኞቻችን፣ በኪነ ጥበብ ባለሙያዎቻችን፣ በታሪክ ተመራማሪዎቻችንና አንጋፋ ፀሐፍቶቻችን ያለማቋረጥ ተዘምሮለታል፤ ተዘፍኖለታል፤ ተፅፎለታል፤ ተተርኮለታል። በአጠቃላይ፣ የአፍሪካ የውኃ ማማነታችንን " Ethiopia, the water tower of Africa!!" በሚል የማንነት አሻራችንን በዓለም ላይ ያተመና ሌላም ብዙ የተባለለት፣ ተፈጥሮ በፀጋዋ የቸረችን ታላቅ ወንዛችን ነው — አባይ!!!

ከላይ "ቁጭት" የሚል ሥነ ልቦናን መሠረት ያደረገ ስሜት ገላጭ ቃል ተጠቅሜያለሁ። ለምን? መልሱ ኢትዮጵያዊ ለሆነ ሁሉ አጭርና ግልፅ ነው። እንደ ወንዙ ባለቤትነታችን መጠቀም አለመቻላችን፣ በተፃራሪው መራባችን መጠማታችን ነው ምንጩ "የአባይን ልጅ ውኃ ጠማው" ብቻ ሳይሆን ልማት ናፍቆን ተርበንና ታርዘን መኖራችን - በአጭሩ የቆየ ድህነታችን ነው የቁጭቱ ሰበብ - ነገር።

ገጣሚ ሞገስ ሃብቱ "አባይ ጠላ ቢሆን"ን የገጠመውና ሁላችንም ጠጥተነው በሰከርን ያለው ወዶ ሳይሆን አባይ ወደ ልማት ተቀይሮ የማየት ህልሙ አልሳካልህ ቢለው ነው። ዛሬስ? ዛሬ ይህ የቁጭት ዘመን የነበረው ላይመለስ ተዘጋ፤ በምትኩ ሌላ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ። ኢትዮጵያ "በሕዝብ ተሳትፎና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፤ ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ ነው" ስትል የሰነቀችውን ራዕይ ዕውን ለማድረግ ከያዘቻቸው ዕቅዶች የአንዱና ግዙፉ ግድብ ብስራት።

ከአንድ የህይወት ምዕራፍ ወደ ሌላ አዲስ ምዕራፍ መሸጋገር የኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ዐቢይ አካል ነውና ይህ ሽግግር በሀገራችንም እውን ሊሆን በቃ፤ አባይ ወደ አገሩና ወገኑ ይፈስ ዘንድ መሠረቱም ተተከለ። የ"ታላቁ ህዳሴ ግድብ" የመሠረት ድንጋይ ተተከለ በይፋ!!! ጊዜው፣ ለኢትዮጵያ፣ የትራንስፎርሜሽን ወቅት ነውና አባይም የዚሁ ዕቅድ አካል ሆኖ ትራንስፎርም አደረገ። ካለማልማት ወደማልማት ተሸጋገረ - ከሰሞኑ የአገር ውስጥና የውጭ የዜና አውታሮች በሰበር ዜናዎች በአግራሞት፣ አድናቆትና ጥልቅ ጉጉት አባይን እያወሱት ነው።

በበርካታ አገራዊ ጥናቶች፣ ትውፊቶች (በተለይ የኪነ ጥበብ ውጤቶች) በተደጋጋሚ እንደተጠና - ተነገረ - ተዜመ፡፡ አባይ ከፍተኛ የሆነ ዕምቅ ኃይል ያለው እየተባለ፣ ድምፃዊት ገነት ማስረሻ እንዳለችው "ጭስ አልባው ነዳጅ" በኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይልም ሆነ በልማት ዘርፍ ከፍተኛ ጠቀሜታን ሊሰጥ የሚችል የሀገራችን ትልቅ ወንዝ ነው። ይህን እምቅ ኃይል በአንድ ጊዜ ወደ ጥቅም ማምጣት ለማንም ቢሆን ይከብዳል። እኛም ይህ ክብደት በፈጠረው ተፅእኖ ሣቢያ ወንዙን ከመጠቀም ለምዕተ ዓመታት ታቅበን ቆይተናል። ነገር ግን፣ አሁን ሁኔታዎች ሙሉ ለሙሉ ተለውጠው አሮጌው ምዕራፍ ተዘግቶ አዲስ ምዕራፍ ተከፍቷል፤ አባይን የመገደብና የመጠቀም አዲስ ምዕራፍ - ድምፃዊት ገነት በወንዙ (ፏፏቴው) ቅላፄ ላይ ተመስርታ "ዛሬ ሰው አገኘህ ስላንተ እሚቆጩ" ስትል እንዳዜመችው ዛሬ ስለ አባይ የሚቆጭ ተቆጭቶም ለልማት የሚነሳ ሰው ተገኘ። አርቲስቶችን በአሁኑ ሰዓት የቀድሞ ቁጭታቸውን ለመወጣት ቆርጠው መነሳታቸው ሰበቡ ይኸው ነው።

## <u>መለምን አስፈለገ? ከግድቡስ ምን ይገኛል? ገደቡ</u>

ከሱዳን ከ20 እስከ 40 ኪሎ ሜትር ወደ ኢትዮጲያ ገባ ብሎ በቤንሻጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ የሚገነባው የህዳሴ ግድብ 5250 ሜጋ ዋት ኃይል ለማመንጭት የሚያስችልና ከ62 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር በላይ ውኃ የመያዝ አቅም አለው፡፡ ግድቡ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ሲጀምርም የአገሪቷን የኃይል አቅርቦት ከሦስት እጥፍ በላይ ያሳድጋል ተብሎ ይታመናል - በጥናቱ እንደተረጋገጠው።

ይህ ነው እንግዲህ የሚሊኒየሙ ግዙፍ የህዳሴ ግድብ ጠቀሜታ። ይህ ማለት ግን ይህ፣ ከግድቡ የሚገኝ ዕምቅ ኃይል ኢትዮጵያን ብቻ ተጠቃሚ ያደርጋል ማለት አይደለም። በፍፁም። በአንፃሩ ሁሉንም (ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን በ1964 ዓ.ም አባይን "የጥቁር ዘር ብስራት" እንዳለው) አጎራባች አገሮች በተለይ ሱዳንና ግብፅን ተጠቃሚ ያደርጋል። ነገር ግን ይህን "ውኃ የጋራ ነው፤ የማንም አይደለም።"
( Abay is belongs to all; and belongs to none.) የሚለውን በጥናት የተደገፈ ፅንሰ ሃሳብ በመረዳት፣ እውነታውን በደስታ የተቀበሉና ቀደም ሲል የነበራቸውን ፅንፈኛ አስተሳሰብ የቀየሩ ወገኖች የመኖራቸውን ያህል በዚያው "አባይ የግላችን ነው" በሚል በአክራሪ አቋማቸው የፀኑና የጦርነት አዋጅ ለመጎሰም የሚቃጣቸው፣ ከዘመኑ አስተሳሰብ ፍፁም ያፈነገጡ አንዳንድ ወገኖች የሉም ማለት ግን አይቻልም። ለዚህ አባባላችን ሰሞኑን ለንባብ የበቁ የሚዲያ ዘገባዎችን በተለይም የግብፅ ፕሬሶችን መጥቀስ ይቻላል።

የአመለካከት ለውጥ (Transformation of Understanding) ካመጡት /ካደረጉት እንጀምር። በነገራችን ላይ ግብፅ ከዓለም ሀገራት ሁሉ ደረቅ ነገር ግን የውኃ ቆጣሪ እንኳን የሌላት ውኃ አባካኝ (ዕድሜ ለዓባይ) አገር መሆኗን እዚህ ላይ ማስታወሱ ተገቢ ነው።

አልመስሪ የተባለው የግብፅ ጋዜጣ ሰሞኑን ባወጣው ዘገባ የቀድሞው የግብፅ የህግ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ሙፊድ ሸሀብና ሌሎች መቶ የሚሆኑ የግብፅ የውኃ ባለሙያዎች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችና በርካታ ሚኒስትሮች የተገኙበትን ስብሰባና ውሳኔዎቻቸውን ጠቅሶ ተሳታፊዎቹ "የግብፅን ብሔራዊ የውኃ መብት ማስከበር እንደሚገባ ሆኖም ግን ወታደራዊ አማራጭን በመተው ከአባይ ተፋሰስ አገራት ጋር ያለውን ትብብር በማክበር አስፈላጊነት [በቅርቡ ኦፊሼያል ያደርጉታል ብለን እናስባለን] ላይ ተስማምተዋል።" ካለ በኋላ ሲቀጥልም "የግብፅ ዓለም አቀፍ የውኃ ኤክስፐርት ዶክተር መጋዊሪ ሸሃታ ዲያብ 'በውዝግቡ ላይ ህጋዊ የሆኑ አካሄዶችን መምረጥ ለዘላቂ መፍትሔ ያዋጣል፤ የአባይ ተፋሰስ አገራት አዲስ ሰነድ መፈረሙም አለመፈረሙም ችግር ያለበት ቢሆንም ግብፅ አንዳንድ

ሁኔታዎችን በማስቀመጥ በስምምነቱ ላይ ብትፈርም የተሻለ ይሆናል።'" የሚሉትን የለውጥ አንፀባራቂ አስተያየቶች ከላይ የጠቀስነው የግብፅ መንግሥት ልሣን የሆነው ጋዜጣ በዝርዝር ያስነብበናል። ከነበረው የውኃ ሞኖፖሊ ግትር አቋማቸው መላቀቅና ወቅቱ ወደሚጠይቀው የለውጥ ጎዳና መምጣት ያልቻሉትን ጥቂት ግለሰቦችን ነውጠኛ አመለካከትም ይኸው ጋዜጣ በስፋት እንደሚከተለው አስነብቦናል። ለመጥቀስ ያህል:-

"ቆራጥ እርምጃ ካልተወሰደ በስተቀር ኢትዮጵያ በጀመረችው የተናጠል እርምጃ ልትቀጥል ትችላለች። ኢትዮጵያ የታችኛው የአባይ ተፋሰስ ሀገሮች ሳያውቁት በሱዳን ድንበር አካባቢ ታላቁን የሚሊኒየም ግድብ ለመገንባት በተናጠል መወሰኗን እንቃወማለን።" ወዘተ የመሳሰሉትንና እዚህ ግቡ የማይባሉ ራስ ወዳድ የውኃ አጠቃቀም (monopolization) አስተሳሰቦችን እናነባለን። በዓመት 21 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር የዓባይ ውኃ እንደሚባክን ያለመረዳትና" ኢትዮጵያ ለምን ከችግር ትላቀቃለች" የሚል ደዌ የተጠናወተው አስተሳሰብ። ሲበዛ አስገራሚ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሰሞኑን ወደ አዲስ አበባ የመጣው የግብፅ የማኅበረሰብ ልዑካን ቡድን በግድቡ መሰራት ላይ ሙሉ በሙሉ ተስማምቶ መመለሱ የኢትዮጳያን ርምጃ ትክክለኛነት በእጅጉ ይገልፃል።

ወደዲያስፖራው (ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያን) ስንመጣም የምናገኘው ተመሳሳይ (የድጋፍና ተቃውሞ) አስተያየቶችን ነው። በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ለሚገኙ ትወልደ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያን ታላቁን የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት አስመልክቶ ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ በተለያዩ የመረጃ መረቦች በቀረበላቸው ጥያቄ መሠረት 78 በመቶዎቹ የግንባታውን ዕቅድ እንደሚደግፉ በከፍተኛ አድናቆት ገልፀዋል፡፡ ቀሪዎቹ ተቃውመውታል ፖለቲካዊ ገፅታ በመስጠት። ግን ለምን?

ይህ ዓይነቱን ራስን፣ የራስ ወገንን፣ በአጠቃላይ የራስን አገር የማጥፋት ተግባር፣ እንደ ባለሙያዎች አገላለፅ Suicide ይባላል። ያም ሆነ ይህ፣ ድምፃዊት ገነት

እንዳለችው "የሚቆጣም ካለ ያበጠው ይፈንዳ" እንጂ ግድቡ ተጠናቆ የኢትዮጵያ ራዕይ ዕውን ይሆናል።

ከላይ ከቀረቡት አብላጫዎቹ አዎንታዊ አስተያየቶች፣ የግብፅ ባለስልጣናትም ሆኑ ትውልድ ኢትዮጵያውያን፤ የምንረዳው አቢይ ጉዳይ ቢኖር የኢትዮጵያ መንግሥት ውሣኔ ትክክለኛ፣ ፍትሃዊና ተገቢ መሆኑን ነው። ድምፃዊት "ዛሬ ሰው አገኘሁ ..." ነው ያለችው??

አርቲስት ስለሺ ደምሴ (ጋሽ አበራ ሞላ) በለሆሳስ ዜማው ትዝታ?፡ አባይን ከአድዋ አርበኞች ጋር በማያያዝ ይመስለኛል፣ ከጣና ሐይቅ የተወለደ የኢትዮጵያ ልጅ መሆኑን (እንደገና) ካረጋገጠ በኋላ ፀጋዬ ገብረ መድህን በበኩሉ "የጥቁር ዘር ብሥራት" እንዳለው "የአፍሪካ ልጆች መጡ እንደገና" ሲል የግድቡን መገንባት አይቀሬነትና የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት (አባይን መገደብ መቻል ከዳግም የአፍሪካ /ጥቁር ህዝቦች ተምሣሌነት ጋር እያወዳደሩት በዜማም በግጥምም ያነሳሱታል፡፡

በሀገር ፍቅር የተንገበገበችው እጅጋየሁ (ጂጂ)ም አባይን "ሽንጣሙ ጋላቢ"፣ "የሞኝ እንባ"፣ "ወገን ጥሎ ሂያጅ" - - - [ነህ] ካለችው በኋላ የመጨረሻውን ምዕራፍ መዝጊያና የመጀመሪያውን ምዕራፍ መግቢያ/ መክፈቻ "አሁን በቃህ፣ ያ ተረት አለፈ" ስትል ያለፈውን አጠቃላ አዲሱን ምዕራፍ ትከፍታለች።

ይህ የጂጂ ዘፈን ኢትዮጵያ ላለፉት ከ10 ዓመታት በላይ (ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ) ለናይል ኢኒሼቲቭ መመስረት አስፈላጊነት፣ የቀድሞውን በአባይ ወንዝ አጠቃቀም ላይ ተደርሶ የነበረው ኢፍትሃዊ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እንዳሉት "የቆየ ማነቆ" ውሣኔ ተረትነትና የአዲስ ስምምነትን አስፈላጊነት - እሰከ አሁኑ ግዙፍ የአባይ ወንዝ ግድብ ግንባታ ድረስ - ያለውን በኪነት /ፈጠራ ዓይኗ አይታ ከላይ የጠቀስንላትን ዘመን ተሻጋሪ አንጓ አዚማለች።

አባይ ይህ ሁሉ ተብሎለታል። ያም ሆነ ይህ አባይ ብዙ ታሪክም አሳልፏል። አሁን ግን አዲስ ምዕራፍ ላይ ይገኛል። ኢትዮጵያውያንም ልክ እንደ አባቶቻችን የጀግንነት ውሎ በልማቱ ዘርፍ ድል ለማስመዝገብ፣ ታሪክ ለመሥራት፣ ድህነትን ከስሩ ፈንቅሎ ለመጣል ከውስጥም ከውጭም ሆ!! ብለው ተነስተዋል። ድፍን ዓለም በጀግንነታችን "አንቱ" እንዳለን ሁሉ በልማቱም ይደግመው ዘንድ "የምናስገድድበት" ጊዜ ቢኖር አሁንና አሁን ብቻ ነው።

ለደንቡ ያህል ከላይ ያሉትን አስተያየቶች እንጥቀስ እንጂ ጉዳዩ የኛና የኛ የኢትዮጵያውያን ብቻ ነው። ለዘመናት ስንቸገር፣ አቁፋዳ ይዘን ለብድር አገር ለአገር ስንዞር፣ ስንለምን . . . የመኖራችን ቁልፍ ምስጢር፣ ባለውኃ ሆነን ውኃን ተንተርሰን ውኃ ላይ መተኛታችን ወዘተ ምኑ ቅጡ ዝርዝሩ ብዙ ነው። ባጭሩ ቀደም ሲል የጠቀስናት ድምፃዊት እያንገፈገፋት እንዳዜመችው መሳቂያ "መሳለቂያ መሆኑ" ይብቃን፤ ይቁም!!!

40 ኪ.ሜ በ40 ኪሜ ስፋትና 145 ሜትር ከፍታ ያለውን የግድብ ዕቅድ ወደተግባር በመቀየር አባይን የተንጣለለ ሜዳ ማስመሰል የእኛ የአሁኑ ትውልድ ድርሻ ነው። ይህ አቅም፣ 5250 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም፣ አሁን ባለን አቅም ላይና ወደፊት ከሚገነቡት አራት ግድቦች ጋር ተዳምሮ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅማችንን የቱን ያህል ሊያሳድገው እንደሚችል ለማንም ግልፅ ነው። ከውኃ ልማቱ፣ ቀደም ሲል እንደጠቀስነው፣ ጎረቤት አገራትም የልማቱ ተጠቃሚ መሆናቸውን ጨምሮ።

በአጠቃላይ፣ ይህ የአገር ኩራት፣ ሲሳይ፣ አባት፣ አለኝታ . . . ለዘመናት ለም አፈራችንን ይዞ ሲሄድ የኖረውን ያህል

አባይ ስም ነው እንጂ ምን ሰርቷል ለአገሩ፣
ትርፉ ለሌላ ነው ሄዶ መገበሩ።

እንደተባለው ማለት ነው፣ ዛሬ ግን አፈራችንን ሊያለማ ቆርጦ ተነስቷል፣ ከጥፋት ኃይልነት ወደልማት ኃይልነት መለወጡ የኛ የኢትዮጵያውያን ድርሻ (በተጠቃሚ

ሀገራት የጋራ መዋእለ ነዋይ /Joint Investment/ መሆን ሲገባው) ሆኖ ከፊታችን ተደቅኗል። ስለዚህ ፣ አጀንዳው የጋራ አጀንዳ፣ ፕሮጀክቱም ለመጪዎቹ ተውልዶች መሠረት የሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ፕሮጀክት እንደ መሆኑ መጠን፣ ሁላችንም - ያገሩን በሬ ባገሩ ሰርዶ እንዲል ሥነ ቃላችን - አብረን ተባብረን በመንግሥት የቀረበውን የታላቁን የሚሊኒየም ግድብ በተያዘለት የጊዜ ገደብ ይጠናቀቅ ዘንድ ታሪካዊ ኃላፊነታችንን እንወጣ "የረሀብ ምንቸት ውጣ፤ የጥጋብ ምንቸት ግባ" መሪ ቃላችን ይሁን። ለዚህ ጥረታችን የጎረቤት/ወዳጅ አገራት ትብብርም አይለየንም ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም ግድቡ ዓላማ ያደረገው የጋራ ተጠቃሚነትን በመሆኑ።

የዕቅዱ ተቃዋሚዎችንም የግድቡን ዓላማ ግራና ቀኝ በማምታታትና አጓጉል ትርጓሜን በመስጠት ውዥንብር (War of understanding) ከሚነዙ ልቦናውን ሰጥቷቸው በራሳቸው ላይ Transformation of understanding በማካሄድና የግንዛቤ /ለውጥ በማምጣት/ ወደ ደሀው ህዝብ በመመለስ በዚህ ግዙፍ (ከአለም ዘጠነኛ ደረጃ ላይ ነው የሚገኘው) ዕቅድ ተሳታፊ በመሆን አሻራቸውን ቢያኖሩ (ሀውልታቸውን ቢተክሉ) መልካም ነው።

ከእንግዲህ አባይ ግንድ ይዞም ሆነ ለም አፈራችንን ተሸክሞ አይሄድም። የ"አፈራችሁን ያዙልን"ም ሳቅ - ስላቅ ከእንግዲህ ተረት ይሁን። "እስከ መቼ?" ሲሉ የሚጠይቁት ሀብረ ዘማሪያን እንዳሉት - አንድ ድንጋይ እንጣል። አለበለዚያ አንድ ጋዜጣ በቅርቡ እንዳስነበበን፣ "ይህን ዕቅድ መቃወም የድንቁርናዎች ሁሉ ድንቁርና ነው" የሚሆነው። አራዶች እንደሚሉት ደፍሞ ሼም ነው። ከሼምም ሼም፡፡